# “ፋኖ’ ሆነን ‘ሞረሽ” ብለን ለኢትዮጵያ

ከበላይ መታፈሪያ(ዶ/ር)

ፋኖ ሆነን ሞረሽ ብለን፣
በኢትዮጵዊነት ተጠራርተን፣
በህዝብ አንድነት ለክብራችን፣
ክተት ብለን ለትስስር ለነፃነት ፍቅራችን፣
እንነሳ ሆ ! ብለን ፍራት ትዕግስትን አሸንፈን
እንደራጅ ለኢትዮጵያ ለብሄራዊ ማንነታችን
አገር ህዝብን ለማዳን፣ ለአንድነቱ ዜግነታችን
**ፋኖ ሆነን ሞረሽ ብለን** **ለኃይላችን**
**ሞረሽ ብለን ፋኖ ሆነን** **ለድላችን።**

የወያኔ-አነግ/ኢህአዴግ ግፍ ጭቆና አረመኔ ሥርዓት
የዘር፣ ቋንቋ ፖሊሲ በሔር-ብሔረተኝነት፣
ጎጠኛ አምባገነናዊ እብሪት፣
ታሪክ አራካሽ ከፋፋይነት፣
ጥላቻ፣ መለያየትን ሰብኰ በቅጥፈት፣
ህዝብን አናካሽ ግጭት ነው እልቂት።

መሰረታቸው ጥላቻ ክፋት፣
ውሸት፣ ክህደት ነው ሥራቸው ቅጥፈት፣
ሌቦች አታላይ አገር ሻጭ መሬት ፣
ትውልድን ገዳይ ብሔራዊ ማንነት።

ፋኖ ሆነን እንታገል በይፋ በተገኘው በአለን ችሎታ፣
ሞረሽ ብለን ተባብረንም ተከባብረን በአመኔታ፣
ሳይውል ሳያድር በትዕግስት በችሎታ፣
ኮሎኔል አብይ ቅጥፈት፣ ስብከት አያታልህ አትገታ፣
እናሶግድ በቶሎ ኢህአዴግ/ ወያኔ-አነግን የዘር በሽታ፣
የባንዳና የተገንጣይ የከፋፋይ ሥርዓትን አሉባልታ
በኢትዮጵያዊነት ሞረሽ ብለን በኢምቢልታ፣
ፋኖ ሆነን ለህዝብ ተስፋ፥ ለአገር አለኝታ።

አገራችን ተደፍራለች፣ ህዝባችንም ተዋርዷል፣
አንይናችንን ጨፍነን፣ እጃችንንም አጣምረን፣በሜጫ በገጀራ ስንገደል ፣

ወጣት ልጆ ሲታገቱ፣ከፎቅም ላይ ሲጣሉ፣ ህዝብ ሲፈናቀል፣
ምንድነው ዝም፣ ምንድነው ትዕግስት አለመታገል
ከእንግዲህ በቃን ዝም አንበል፣
በአገር ወዳድነት እንነሳ ሞረሽ ብለን ይቻላል፣
ለአገር ክብር እንታጠቅ፣ እንታገል
**ፋኖ ሆነን፣ ሞረሽ ብለን ለኃይል፣**
**ሞረሽ ብለን ፋኖ ሆነን ለኢትዮጵያዊነት ድል።**

አይደለም ወግ አይደለም ባህል ለሕዝባችን፣
በባንዳ ልጆች-በተገንጣይ ጽንፈኞች ተገዥነት ለክብራችን፣
አገር ለማፍረስ በሄር-ብሄረሰብ ስንባል ሲለያዮን፣
አንድነታችንን ከፋፍለው ሲያጠፉና ሲገሉን፣
በተናጠል ከምንጠፋ፣ በቤሔራዊ ማንነት ክብር እንዳን።
እናስጨንቅ ዘረኛን፣እናሸብር ጠላትን፣
እንበታትን እናውድመው ጦረኛን። **“ሞረሽ ብለን ፋኖ ሆነን”**

አገር ክብርን ላለማስደፈር ነፃነት፣
በተረጋጋ ታሪካዊ ትግል ስልት በመነሳት፣
መላ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በአንድነት
ለበሔራዊ ሰላም ፍቅር ደህንነት፣
“በጀግና ፋኖ አርበኞች” ወሳኝ ሚና ተዋናይነት፣
ለእናት አገር ኢትዮጵያችን በህብረት፣
ለብሔራዊ ድል መሰረት፣ ለማይበገር ክብርና ኩራት።
ፋኖ ሆነን እንነሳ ፣ እንሰማራ ሁላችን በአርበኝነት፣
ዘረኛ ባንዳ ወራሪውን፣ተገንጣዩን **ድል ለመንሳት።**

**በኢትዮጵያዊነት እንነሳ ሞረሽ ብለን ይቻላል፣**
**በአገር ወዳድነት እንሰማራ ፋኖ ሆነን ለድል።**

አገር ህያው ናት ፈጽሞ አታልፍም፣
ጠባቂ አላት ታሪክ ሰሪ ምንጊዜም፣
ትውልድ አለ በዘመኑ መልካሙንም የሚሰራ፣
በኢትዮጵያዊነቱ እጅግ በጣም የሚኮራ
የአገር ኩራት ታሪክንም የሚያራምድ፣
የመልካ ሥራ ቀጣይ ትውልድ፣
የታሪኩ መሀደር የየትውልዱ መኩሪያ፣
ለእናት አገር ክብር ኩራት ለኢትዮጵያ።